የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲ ቀን ፪ሺ፲፩

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 55
ADDIS ABABA, 18th April, 2019

<u>ማውጫ</u>

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፯ /፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

ለመቀሌ ውሀ አገልግሎት አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ………………......................................ገጽ ፲፩ሺ፪፻፲፮

## CONTENT

Proclamation No. 1137/2019

Export-Import Bank of China Loan Agreement for Financing Mekelle Water Supply Development Project Ratification Proclalmataion....................................................Page 11216

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፯ /፪ሺ፲፩**

<u>**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**</u>

ለመቀሌ ውሃ አገልግሎት አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፩ ቢሊዮን ፸ ሚሊዮን ሪንሚንቢ ዩዋን (አንድ ቢሊዮን ሰባ ሚሊዮን ሪንሚንቢ ዩዋን) ኮንሴሽናል ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል ሰኔ ፮ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በቤጂንግ የተፈረመ በመሆኑ፤

እንዲሁም ለዚሁ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ፭፻፵ ሚሊዮን ሪንሚንቢ ዩዋን (አምስት መቶ አርባ ሚሊዮን ሪንሚንቢ ዩዋን) በቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ በኩል የሚቀርብ ከወለድ ነፃ የሆነ የማዕቀፍ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

**PROCLAMATION NO. 1137 /2019**

<u>**PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND EXPORT- IMPORT BANK OF CHINA**</u>

**WHEREAS**, A Loan Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China under which the Export - Import Bank of China agreed to provide to the Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia a Concessional Loan in an amount of Renminbi Yuan 1,070,000,000 (Renminbi Yuan One Billion and Seventy Million) for financing the Mekelle Water Supply Development Project was signed in Beijing on 13th day of June, 2018;

**WHEREAS**, A Frame Work Loan Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People's Republic of China under which the Government of the People's Republic of China through the Export - Import Bank of China agreed to provide to the Federal Democratic Republic

ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ግንቦት ፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለመቀሌ ውሃ አገልግሎት አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፯/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል ሰኔ ፮ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በቤጂንግ የተፈረመው ቁጥር China Exim Bank GCL No. (2018) 15 Total No. (657) የብድር ስምምነት እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ግንቦት ፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የማዕቀፍ የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

of Ethiopia an interest free Loan in an amount of Renminbi Yuan 540,000,000 (Renminbi Yuan Five Hundred and Forty Million) for financing the Mekelle Water Supply Development Project was signed in Addis Ababa on 10th day of May, 2018.

**WHEREAS**, the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 5th day of April, 2019 ;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia,it is hereby Proclamined as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Export-Import Bank of China Loan Agreement for Financing Mekelle Water Supply Development Project Ratification Proclalmataion No. 1137/2019''

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement Number China Exim bank GCL No. (2018) 15 Total No. (657) signed in Beijing on 13th day of June 2018 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China and the Frame Work Loan Agreement signed in Addis Ababa on 10th day of May 2018 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People's Republic of China is hereby ratified.

**፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩ ቢሊዮን ፸ ሚሊዮን ሪንሚንቢ ዩዋን (አንድ ቢሊዮን ሰባ ሚሊዮን ሪንሚንቢ ዩዋን) ኮንሴሽናል ብድር እና ፭፻፵ ሚሊዮን ሪንሚንቢ ዩዋን (አምስት መቶ አርባ ሚሊዮን ሪንሚንቢ ዩዋን) ከወለድ ነፃ የሆነ ብድር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**3. Power of the Ministry of Finance**

Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Concessional Loan in an amount of Renminbi Yuan 1,070,000,000 (Renminbi Yuan One Billion and Seventy Million) and the interest free Loan in an amount of Renminbi Yuan 540,000,000 (Renminbi Yuan Five Hundred and Forty Million) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 18th day of April, 2019**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**